# መመርያ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ
BOARD OF EDUCATION OF MONTGOMERY COUNTY

ተዛማጅ መመሪያዎች/ደንቦች፡- ABA, ABC, ACA, AFA-RA, EGI-RA, IGS, IKA-RA, ILA-RA, JOA-RA, KBA-RA, KLA, KLA-RA

ኃላፊ ጽ/ቤት፡- ዋና ሃላፊ/Chief of Staff

## ስለ ህዝባዊ መረጃ ፖሊሲ

A. ዓላማ

1. ለት/ቤት ዲስትሪክቶች እና ለማህበረሰቡ አላማዎች፣ ፍላጎቶች፣ እድሎች እና ግዴታዎች አግባብነት ባላቸዉ የተለያዩ ሚዲያ የመገናኛ አውታሮች ዉጤታማ ግንኙነት አማካይነት ስለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የህዝብ ግንዛቤን፣ ድጋፍን፣ እና መተማመን በተመለከተ ራዕይ ማዘጋጀት

2. በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ መርህ መመስረት ተገቢነት ያላቸውን ወቅታዊ እና የተሟሉ መረጃዎችን ለህብረተሰቡ ለማሳወቅ ግልጽ የሆነ፣ እርግጠኛ፣ እና ለማህበረሰብ ተደራሽነት ያላቸው በተቻለ መጠን ገላጭ መረጃዎች ለመስጠት

B. አቋም

1. አክብሮትን፣ እምነትን፣ መተማመንን፣ እና ስለ MCPS የትምህርት ፕሮግራም እና ተግባራት ወጥ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖር ለማበረታታት ቦርዱ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ማህበረሰብ ጋር አመርቂ ግንኙነት ለማስፈን ይፈልጋል

   a) ወላጆች/ሞግዚቶች፣ ተማሪዎች፣ ሠራተኞች እና ሌሎች የማህበረሰብ ባለድርሻ አካላት ስለ ት/ቤት ዲስትሪክት ግቦች፣ ፕሮግራሞች፣ እና ፖሊሲዎች ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማስቻል አግባብነት ያለው ገላጭ አዉድ በወቅቱ እና በተሟላ ሁኔታ መረጃ ማቅረብ፣

   b) በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት በንቃት እንዲሣተፉ ለማበረታታት እና ስለተማሪዎቻቸው፣ የራሳቸውን አመለካከቶች እና ስጋት እንዲያቀነቅኑ ለባለድርሻ አካላት ተገቢውን መረጃ መስጠት፣ እና

   c) በማህበረሰብ አባላት፣ድርጅቶች እና ቢዝነሶች ንቁ ተሳትፎ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ማዳበር።

2. በቦርድ ፖሊሲ "Board Policy ABA" ላይ በተገለጸው መሠረት፣ በእኛ የብዙሃን ማህበረሰብ መካከል ትርጉም ያለው የሁለት ወገን ግንኙነትን ሰፊ ምህዳር ለማበረታታት ቦርዱ በርካታ የተለያዩ የግንኙነት መስመሮችን ይሰጣል የማህበረሰብ ተሳትፎ/Community Involvement። የቦርድ ፖሊሲዎችን ለመገምገም/ክለሳ ለማድረግ፣ ለስትራቴጂ እቅድ፣ ለባጀት ቀመር፣ እና የት/ቤት ዲስትሪክት እቅዶችን ለመተግበር በእኛ የብዛሃነት ማህበረሰብ መካከል ትብብር እና ፍሬያማ የሆነ ግንኙነት የሂደቱ አይነተኛ አካል ነው።

3. MCPS ህዝባዊ መረጃዎችን የመጠበቅ ግዴታ ያለበት እንደመሆኑ መጠን፣ የትምህርት ዲስትሪክቱ ሥራ የሚካሄደው ለህብረተሰቡ መረጃ የመስጠት እና ግልጽ ስብሰባዎችን የማካሄድ ህግጋትን በመከተል ነው።

   a) ቦርዱ ውሎችን/ስምምነቶችን፣ ቅድመሁኔታዎችን፣ እና ከማህበረሰቡ የሚጠበቅበትን የኢንፎርሜሽን ደንብ/Public Information Act of Maryland (MPIA) እና የቤተሰብ ትምህርት መብቶች እና የግል ገመና

ደንብን/Family Educational Rights and Privacy Act (FERPA) ሙሉ በሙሉ ለመጠበቅ/ለማክበር ቁርጠኛ ነው። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የህብረተሰብ ሪኮርዶች ባለአደራ እንደመሆኑ መጠን ስለ ማህበራዊ ሪኮርዶች የሚቀርቡትን ጥያቄዎች በተገቢው ጊዜ እና ሁኔታ ይመልሳል። MCPS የማህበረሰብ መረጃዎችን በአደራ ጠባቂ እንደመሆኑ መጠን፣ በ MPIA፣ FERPA፣ ወይም በሌሎች ተፈጻሚነት ካላቸው ህጎች በአንዳቸው በልዩ ሁኔታ ካልተያዘ በስተቀር፣ ተገቢ መረጃዎችን በሙሉ ተደራሽ ያደርጋል

b) የትምህርት ተልእኮዉን ከግብ ለማድረስ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከተማሪዎች እና ከቤተሰቦች ጋር ግልጽ እና ተአማኒነት ያለው የግንኙነት መስመሮችን መገንባት አለበት። ያንን ለማድረግ፣ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ተፈጻሚነት ካላቸው ህጎች ጋር የሚጣጣሙ ትምህርታዊ ሪኮርዶችን የግል ህይወት እና ሚስጥራዊነት እንደሚጠበቅ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እምነት ማሳደር አለባቸው። በተጨማሪ፣ ሠራተኞቹ፣ ኮንትራክተሮች፣ ተቋራጮች እና አጋሮች፣ እንደዚሁም የውጭ ተመራማሪዎች፣ ስለ መረጃ ማሰባሰብ፣ የግል ጉዳይ፣ እና ደህንነት፣ እንደዚሁም በዚህ ሳይገታ ስለ FERPA፣ the Children's Online Privacy Protection Act፣ the Protection of Pupil Rights Amendment፣ the Maryland Student Privacy Act of 2015፣ እና the MPIA የመሣሠሉ ተፈጻሚነት ያላቸው ህጎችን እንዲያከብሩ MCPS ይጠብቃል/ይፈልጋል።

4. ስለ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት የስራ ክንውን፣ በዚህ ባያበቃም እነዚህን የሚያካትት፣ ለወላጆች/ሞግዚቶች፣ ተማሪዎች፣እና ሠራተኞች ስለ አስቸኳይ/ድንገተኛ ሁኔታ ተፈላጊ መረጃዎችን፣ እንዲሁም የትግበራ መረጃ እየተሳተፉ ላሉ፣ እና የ MCPS ን ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን እና ትግበራዎችን ለመርዳት እንደ አጋር፣ በተቋራጭነት፣ ወይም ፕሮግራም፣ እቃዎችን፣ እና/ወይም አገልግሎቶችን በመስጠት መሳተፍ ለሚፈልጉ MCPS ተገቢ እና ወቅታዊ ግንኙነት ያደርጋል።

5. MCPS ስለ ተማሪዎች፣ ሠራተኞች፣ ወላጆች/ሞግዚቶች፣ እና ሌሎች የማህበረሰብ አባላት ስለ ግል ጉዳይ/ገመና የሚሰጡትን ዋጋ በመገንዘብ መረጃዎችን ለመጠበቅ፣ እና የተማሪ እና የሠራተኛ መረጃ በፌደራል እና በስቴት ህግ መሠረት ሁሉንም ህጋዊ ግዴታዎችን በማክበር አግባብነት ሲኖረው ብቻ ይፋ እንደሚያደርግ ያረጋግጣል።

a) የተማሪና የሠራተኞችን መረጃ ስለመጠበቅ፣ እና ስለ MCPS ድረ-ገጽ አጠቃቀም ግላዊ ስርአት/ፕሮቶኮል እንዲዘጋጅ የትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ ለሠራተኞች መመሪያ ይሰጣል።

b) ቦርዱ ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸው እና ሚስጥራዊነት ያላቸው መረጃዎችን የሚያገኙ ባለድርሻ አካላት በሙሉ ተገቢውን ሥርዓት/ፕሮቶኮል እንዲጠብቁ፣ እንዲጠቀሙ፣ እና/ወይም እንደነዚህ ዓይነት መረጃዎችን በተፈቀደላቸዉ ገደብ ብቻ ይፋ መደረግ እንዳለባቸው ይጠብቃል።

c) ሠራተኞች የተማሪ እና የሠራተኛ ውስብስብ የሆኑ የግል ገመና ሪኮርዶችን እንድምታ በሚመለከት ተገቢ ጥንቃቄ እንደሚያደርጉ እና የተማሪ እና የሠራተኛ መረጃዎችን ህጉ በሚያዘው መሠረት በሚስጥር ለመጠበቅ የሚያስችላቸው በቂ ስልጠና ተሰጥቷቸዋል።

6. MCPS የትምህርት ቤት ዲስትሪክቱን ተልእኮ፣ ግብ፣ ፕሮግራሞች፣ ክንውኖች፣ ፍላጎቶችን በሚመለከት ለማህበረሰቡ ለማሳወቅ እና ለማስገንዘብ በርካታ የግንኙነት መስመሮችን ይጠቀማል።

a) በተቻለ መጠን ህዝባዊ መረጃዎችን ለበርካታ ማህበረሰብ ተደራሽነትን ለማስፋት፣ MCPS –

(1) ስለተደራሽነት የአካል ስንክልና ያለባቸው አሜሪካውያን ደንብ መስፈርትን ይጠብቃል፣ እና

(2) የማስተርጎም አገልግሎቶችን ይሰጣል፣ እና በአብዛኛው የ MCPS ተማሪዎች ወላጆች/ሞግዚቶች የትርጉም አገልግሎት እንዲሰጣቸው በሚጠይቋቸው ቋንቋዎች የማስተርጎም እና ቁልፍ የሆኑ የትምህርት ቤት ዲስትሪክት መገልገያዎችን (resources ) ትክክለኛ የትርጉም አገልግሎቶች ይሰጣል።

b) MCPS አዳዲስ የሚመጡ የመገናኛ ቴክኖሎጂዎችን እንደየአግባቡ ሥራ ላይ በማዋል ይጠቀማል፣ እና ውጤታማ፣ ጥሩ ስነምግባር፣ እና ኃላፊነት የተሞላበት አጠቃቀምን በሚመለከት ለተማሪዎች እና ለሠራተኞች መመሪያ

ይሰጣል።

c) MCPS ለሁሉም ተማሪዎች ምርጥ ትምህርት ለመስጠት የጋራ ተልእኳችንን በሚመለከት ለህብረተሰቡ ለማሳወቅ እና ማህበረሰብ እንዲሳተፍ፣ ድረ-ገጾችን እና የአውታረ-መረብ አገልግሎቶችን ይጠቀማል።

(1) MCPS ድረ-ገጾችን እና የአውታረ-መረብ አገልግሎቶችን የሚጠቀመው ስለ MCPS ለማህበረሰብ መረጃ ለመስጠት እና በዲስትሪክቱ እና በማህበረሰቡ መካከል የሁለት-ወገን ግንኙነትን ለማዳበር ነው።

(2) አብዛኛዎቹ የእኛ ወላጆች/ሞግዚቶች፣ ተማሪዎች፣ ሠራተኞች፣ እና ሌሎች የማህበረሰብ ባለድርሻ አካላት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ድረ-ገጾች እና አውታረ-መረብ አገልግሎቶችን ጠቃሚ/አስፈላጊ መገልገያዎች መሆናቸውን እንደሚያዉቁ ቦርዱ ይገነዘባል፣ ስለሆነም MCPS እነዚህን መገልገያዎች በተገቢነት ውጤታማ፣ ቀልጣፋ እና በአስተማማኝነት የመምራት ጥንቃቄ ያወስዳል።

(3) MCPS ሁሉም ባለድርሻ አካላት ድረ-ገጾችን እና አገልግሎቶችን ኃላፊነት በተሞላበት አኳኋን እንዲጠቀሙ ያበረታታል።

7. በዲሞክራሲያዊ ህብረተሰብ መረጃዎችን በመፈለግ፣ በመተንተን፣ እና ስለ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርታዊ ፕሮግራሞች እና አስተዳደር መረጃዎችን ለህብረተሰብ ሪፖርት በማድረግ ሚድያ የሚጫወተውን ኃላፊነት የተሞላበት ሚና ወሳኝነት ቦርዱ ዋጋ ይሰጣል። በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እና የሚድያ ተወካዮች መካከል ፈጣን፣ ውጤታማ፣ እና ኃላፊነት የተሞላበት ግንኙነት እንዲኖር የትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ ተገቢውን ሥርዓት/ፕሮቶኮል ያበጃል።

## C. ተፈላጊ ውጤቶች

ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እና ከማህበረሰብ ዓላማዎች፣ ፍላጎቶች፣ እድሎች፣ እና ግዴታዎች ጋር የሚጣጣሙ የተለያዩ ዓይነት የመገናኛ ብዙሃንን በሚመለከት ግንዛቤ እንዲኖር፣ ድጋፍ፣ እና ጥሩ ግንኙነት በመዘርጋት ስለ MCPS መተማመን እንዲሠፍን ለማድረግ MCPS የህብረተሰቡን ግንዛቤ ያዳብራል። ስለ መረጃዎቹ ትክክለኛነት የማረጋገጥ ጥረቱ እንዳለ ሆኖ፣ ወቅታዊ፣ ግልጽ፣ የተጣራ፣ እና በተቻለ መጠን የማብራሪያ ዐውድ ለህዝብ ተደራሽ የሆኑ፣ ተገቢ መረጃዎች በሙሉ በተሟላ ሁኔታ ለማህበረሰቡ ይገለጻሉ።

## D. የአተገባበር ስልቶች

ይህንን ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ የትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ መመሪያዎችን ያዘጋጃል።

## E. ግምገማ-ክትትል እና ሪፖርት

ይህ ደንብ በቦርድ የማሻሻያ መመርያ መሰረት ክለሳ ይደረጋል።

የሚዛመዱ ምንጮች፡- *Family Educational Rights and Privacy Act*, 20 U.S.C §1232g; Protection of Pupil Rights Amendment (PPRA), 20 U.S.C. §1232h, 34 CFR Part 98, (2000 and Supp IV 2004); Section 504 of the Rehabilitation Act of 1973, as amended, 29 U.S.C. Sec 794; *Americans with Disabilities Act* (ADA), 42 U.S.C. 12131 et seq; *Children's Internet Protection Act* (CIPA), 47 U.S.C. §254(h)(5)(B)-(C), 254(l); *Children's Online Privacy Protection Act of 1998 (COPPA), 15 U.S.C.6501-6505*, 16 CFR Part 312; *Public Information Act of Maryland*, Ann Code of Maryland, General Provisions Article §§4-101 through 4-601; *Maryland Student Data*

*Privacy Act of 2015,* Ann Code of Maryland, Education Article, §4-131.

የመመርያ ታሪክ፡- የውሳኔ ቁጥር 24-68 ጃኑወሪ 9/1968፣ በውሳኔ ቁጥር 310-19 ሜይ 14/2019 ተሻሽሏል።

ማሳሰቢያ፡- መረጃን ይፋ ስለማድረግ የቦርድ ፖሊሲ መመሪያዎች (Tenets of Board policy KBB)፣ በውሣኔ ቁጥር 310-19 ተካተዋል፣ የዚህ ፖሊሲ ማሻሻያ እና, የቦርድ ፖሊሲ (Board Policy KBA) ሜይ 14/2019.በተወሰነ ወቅት ተሠርዟል።